# ጠፍቶ እንጂ አዕምሮ

እፉኚት ወያኔ ፣ ሃያ ሰባት ዓመት ፣ አምጦ የወለደው
ይይዘው የጠፋው ፣ ልቡ የደነደነ ፣ ዐይኑን የጋረደው
በኬኛ ተለክፎ ፣ ገራባ እየቃመ ፣ እንዳይሆን ያበደው
በየ ጉራንጉሩ ፣ እያፈናቀለ ፣ ዜጋ የሚያሳድደው
በካራ በሜንጫ ፣ ጭካኔ ተሞልቶ ፣ አጋድሞ የሚያርደው
ለችግር መከራ ፣ የተፃፈ ይመስል ፣ ሸክም የማይከብደው
ምነው ሕዝቤ ተኛ ፣ ደም እየዘነበ ፣ አይሞቀው አይበርደው?
የወያኔው አንጋች ፣ ጅቡ ሲሾልክበት ፣ ውሻው በቀደደው ።

ይኖር የነበረ ፣ በወያኔ ጉያ ፣ ስብዕናው ተዋርዶ
የተነገረለት ፣ ጥበት ያሰከረው ፣ ጭራሽ ወርዶ ወርዶ
ህፃናት አግቶ ፣ ቤተ እምነት አቃጥሎ ፣ ካህናትን አርዶ
ኮሌጅ ሲያል ሆኖ ፣ በነጋ በጠባ ፣ እያሰማን መርዶ
የሚሲዮን አረም ፣ ታሪኩን የረሳ ፣ ቅል የሆነ ባዶ
ዕድል ከቸረችው ፣ መግባባት ተስኖት ፣ እንዳይኖር ተላምዶ
መገንባትን ባያውቅ ፣ ትውልድ ያቆየንን ፣ ያፈርሰዋል ንዶ ።

የአብሮነትን እሴት ፣ በፈጠራ ትርክት ፣ ደልዞ እያጠፋ
በጎጥና በዕምነት ፣ ሕዝብ እየከፈለ ፣ ጥላቻ እያስፋፋ
አገር ሲተራመስ ፣ መምራት የተሳነው ፣ ካለፈው የከፋ
ዛሬም እንደ ትላንት ፣ ፋሽስቶችን አዝሎ ፣ መከራ እየገፋ
ሞቶ ያመጣው ለውጥ ፣ ታጥቦ ጭቃ ሲሆን ፣ ስትጨልም ተስፋ
አንገት በማቀርቀር ፣ ወይም በማባበል ፣ ችግሩ ላይጠፋ
እንደ ደገሙበት ፣ በጥቁር ሰማይ ስር ፣ አለ እያንቀላፋ ።

በግራም በቀኝም ፣ ፅንፈኞች ባስነሱት ፣ ስንት ደም ፈሰሰ ?
በመንጋ ጋጠወጥ ፣ ስንት አጥንት ተሰብሮ ፣ ስንት ተከሰከሰ ?
ስንት ንብረት ወድሞ ፣ ስንቱ ተንገላታ ፣ ስንቱስ አለቀሰ ?
አበጀ አሉት እንጂ ፣ ማን ተጠየቀበት ፣ ማንስ ተከሰሰ ?
መአት ሲዘንብበት ፣ ማን ደርሶ አፅናናው ፣ ማነው የደረሰ ?
ያሁኑ ይባስ እንጂ ፣ ገዳይ ተወድሶ ፣ ሟቹ ተወቀሰ ።

በዘመነ ኦነግ ፣ በዘመነ ኦዴፓ ፣ የማናውቀው ኑሮ
ሰውን እንደንሰሳ ፣ አርደው የበሉቱ ፣ የሚቀፍ ለጆሮ
ዜጋው በሐገሩ ፣ እንደ ስደተኛ ፣ አንገት አቀርቅሮ
በፅንፈኞች ቀንበር ፣ አይደለም እጅ እግሩ ፣ አንደበቱ ታስሮ
እንኳንስ የሰው ልጅ ፣ ምድር ብታወራ ፣ አፍ ቢኖራት ኖሮ
የወላድ መካኗ ፣ የናት ኢትዮጵያ ፣ ለቅሶዋና እሮሮ
መች እረፍት በሰጠን ፣ ዛሬ ነገ ሳንል ፣ ባላሻም ቀጠሮ
ማስተዋል እርቆን ፣ እራስ ወዳድ ሆነን ፣ ጠፍቶ እንጂ አዕምሮ ።

ታዛቢው

February 26, 2020